# የ ሰ ላ ም ት ግ ሉ በ ኢ ት ዮ ጵ ያ (ክፍል ፪ - ሁለተኛው ጉዳይ)

አንዱዓለም ተፈራ - የእስከመቼ አዘጋጅ
ሰኞ፤ ሐምሌ ፳ ቀን፤ ፳፻፯ ዓመተ ምህረት ( 7/27/2015 )

## በአንድነት ተሰባሰበን እስካልታገልን ድረስ፤ ትግሉ ሕዝባዊ አይደለም፤ ድሉም የኢትዮጵያ ሕዝብ አይሆንም።

በክፍል ፩ የመጀመሪያው ጉዳይ ላይ፤ ከየት እንጀምር የሚለውን በአጠቃላይ ቃኝቸዋለሁ። በዚህ በሁለተኛው ጉዳይ ደግሞ፤ በተደጋጋሚ በኢትዮጵያዊያን ድረገጾች እየተመላለስኩ እንድጽፍ ያደረገኝን፤ በአንድነት ተሰባስበን መታገሉን አጎላዋለሁ። በአንድነት ተሰባሰበን እስካልታገልን ድረስ፤ ትግሉ የኢትዮጵያ ሕዝብ ትግል አይደለም። በዚህ ትግል የሚገኘው ድልም የኢትዮጵያ ሕዝብ ድል አይሆንም። **“ብቻ የትግሬዎች ነፃ አውጪ ግንባር መንግሥት ይውደቅ እንጂ!”** የሚለው ጭፍን እምነት፤ የወደፊቷን ኢትዮጵያና የፖለቲካ ሀ - ሁ ን ያላገነዘበ ነው። ይህ **“የኢትዮጵያ ሕዝብ፤ ከባርነት ለመውጣት የሚያደርገው የነፃነት ትግል ነው!”** በማለት በተደጋጋሚ አስምሬያለሁ። ታጋዩም መሪውም ሕዝቡ ካልሆነ፤ የነፃነት ትግል አልተያዘም። ዋናው ትኩረታችን በዚህና በዚህ ላይ ብቻ ካልሆነ፤ የሽቅድድም ጉዳይ ይዘናል ማለት ነው። በምንም ዓይነት ይሁን በምንም፤ ማንም ድርጅት ለብቻው የሚያደርገው ትግል፤ የወገንተኛውን አምባገነን የትግሬዎች ነፃ አውጪ ግንባር መንግሥት ተክቶ፤ ራሱ ገዢ ለመሆን እንጂ፤ የሕዝቡን የነፃነት ጥማት ከግቡ ለማድረስ አይደለም።

ባለፉት አርባ ዓመታት፤ የሚቀጥለው መንግሥት የተሻለ ይሆናል እያልን፤ ከነበረው የባሰ እየመጣ፤ የሕዝቡ የኑሮ ሁኔታ ከመቼውም በከፋ ደረጃ ወደታች እየዘቀጠ፤ መቀጠላችን ሀቅ ነው። አሁንም እያንዳንዱ ድርጅት የያዘው፤ ገዥውን ድርጅት በሌላው ለመተካት ከሆነ፤ ትግሉ የተተኪው ድርጅት እንጂ፤ የኢትዮጵያ ሕዝብ ትግል አይደለም። በርግጥ ማንም ድርጅት ሊመሠረትና፤ ለተመሠረተበትና በመርኅ-ግብሩ ላሠፈረው ዓላማ ሊታገል ይችላል። ያንን ማንም ሊያቆመው አይችልም። ያ ትግል ግን፤ የዚያ ድርጅት ትግል ብቻ መሆኑ፤ መታወቅ አለበት።

በአሁኑ ሰዓት፤ የኢትዮጵያ ሕዝብ ለነፃነቱ የሚያደርገውን ትግል አብሮ በአንድነት ከጎኑ መቆም፤ ድሉ የራሱ የሕዝቡ እንዲሆንና ይህን ሊያደናቅፍ የሚነሳውን መቃወም፤ የያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ ታጋይ ግዴታ ነው። በሀገርና በድርጅት መካከል ያለውን ልዩነት የማያውቅ ኢትዮጵያዊ የለም። ይህን በድፍን መናገር እችላለሁ። ታዲያ ለሀገር የሚደረግ ትግልና ለድርጅት የሚደረግ ትግል፤ የተለያዩ መሆናቸውን መረዳቱ ከዚሁ ይመነጫል። ድርጅቶች በሙሉ፤ የትግላቸውን ሂደት በትክክል ለመምራት፤ የተግባር ቅደም ተከተላቸውን ማወቅ አለባቸው። እናም አሁን የሀገር ነፃነት በተያዘበት ትግል፤ የድርጅቶች የራሳቸው ብቻ የሆነ ጉዳይ፤ ወደኋላ መጎተት አለበት። ደግሞ ድርጅት የሚመለክ ጣዖት አይደለም። ድርጅት መሣሪያ ነው። መሣሪያ ደግሞ፤ እንደ መገልገያነቱ፤ በወቅቱና በቦታው አስፈላጊ የሆነው ብቻ ነው የሚነገበው። ዛፍ ለመቁረጥ ዶማ፤ መሬት ለመቆፈር መዶሻ ተይዞ አይወጣም። ሀገርን ነፃ ለማውጣት፤ ሀገር አቀፍ ሕዝባዊ ንቅናቄ ነው የሚያስፈልገው።

በርግጥ ይህ በአንድ ጊዜ ሊቆቹ በጠረንጴዛ ዙሪያ ተቀምጠው የሚወስኑት ጉዳይ አይደለም። በሀገራችን በኢትዮጵያ፤ የደረሰባቸውን በደል በመቃወም፤ በተለያየ መንገድ፤ በተለያየ ወቅት፤ የተለያዩ ታጋዮች፤ የተለያዩ ድርጅቶችን መሥርተው ትግል ጀምረዋል። ይህ በተጨባጭ ያለና የማይካድ ሀቅ ነው። አሁን እኒህ ሁሉ ድርጅቶች፤ ዋናው ሀገራዊ ነፃነት መሆኑን ያውቃሉ። ታዲያ ለሀገራዊ ነፃነቱ፤ በብዛት ሕዝቡ በአንድነት የሚሰባሰብበት፤ አንድነት ያለውና በሀገራዊ ነፃነቱ ላይ ያተኮረ ንቅናቄ መመሥረቱን፤ ቅድሚያ ሊሠጡት ይገባል። ቅድሚያ ለዚህ ሠጥተው፤ በአንድነት ለመታገል፤ የየድርጅት ግላዊ ዓላማቸውን፤ ለሀገር ነፃነት መሰዋዕት ማድረግ አለባቸው።

አንዳንድ ድርጅቶች በያዙት መንገድ ለመግፋት የሚያቀርቡት መመከቻ፤ **“ሌሎችን ቁጭ ብዬ አልጠብቅም። ቢመጡ ይምጡ፤ እኔ ግን መቀጠል አለብኝ! እኔን ብቻ እመኑኝ። ሌሎቹ አይረቡም!”** ነው። ሌሎች ደግሞ፤ **“ሁሉም በመረጠው ቢታገል፤ እኛ ምን አገባን! ዝም እንበል!”** ይላሉ። እንዲሁም ሌሎች፤ **“ለምን ተቃዋሚን እንቃወማለን?”** በማለት የሚነቅፉ አሉ። ይህ ትግል የሀገር ነፃነት ትግል ነው። ይህ ትግል የሀገራችንን የኢትዮጵያን ሕልውናና የያንዳንዳችን ኢትዮጵያዊያንን የወደፊት ወሳኝ ነው። የሚቀጥለውን መንግሥት አቋቋሚ ኃይል ነው። ስለዚህ፤ ማንኛውም የትግል ድርጅት የሚወስደው ዕርምጃ፤ እያንዳንዳችን ኢትዮጵያዊያንን ያገባናል። በትግሉ ዙሪያ ያሉትን ጠቅጥቆ ሌሎች ኢትዮጵያዊያንን በሙሉ ለትግል

አስነሳለሁ ማለት፤ ማፌዝ ነው። የሁላችን የሆነውን የሀገራችንን የነፃነት ትግል በአንድነት ማድረጉ፤ አማራጭ የሌለው ስለሆነ፤ ከያዝነው ተግባር ይልቅ፤ በአንድነት ለመነሳታችን ቅድሚያ መሥጠቱ፤ ለትግሉና ለድሉ ስኬት፤ አስተማማኝ ነው።

ታጋዮችን በሙሉ የግድ ወደ አንድ እንድንሰባሰብ የሚያደርገን ምንድን ነው? መጀመሪያ የምንታገልላቸው ዋና ዋናዎቹ ጉዳዮች የጋራ ናቸው። ኢትዮጵያዊያን፤ ከወገንተኛው አምባገነን የትግሬዎች ነፃ አውጪ ግንባር መንግሥት ነፃ ለመውጣት በሚታገሉበት ወቅት፤ በኢትዮጵያዊነታችን፤ አብረን የትግሉ አካል ለመሆን ነው። በሀገራችን ጉዳይ ላይ ኢትዮጵያዊያን አንድ ነን። ትግሉ በዘረኝነት ላይ የተመሠረተ አገዛዝን፣ ብዙዎችን ያገለለውንና በጥቂቶች የሚመራን አስተዳደር ለማስወገድ ነው። ትግሉ የውጪ ሀገር ባለሀብቶች፣ ቡድኖች፣ ሆኑ መንግሥታት፤ በሀገራችን ጉዳይ ጣልቃ ገብነታቸው መክኖ፤ የራሳችን ነፃ መንግሥት እንዲኖረን ነው። ሀገራችን አንድ ናት። ዳር ደንበሯን እንጠብቃለን። ትግሉ ሁሉን ያካተተ፣ የያንዳንዳችን ኢትዮጵያዊያን ዴሞክራሲያዊ መብት የሚጠብቅ፣ የሕግ የበላይነት በሀገራችን በኢትዮጵያ የሚያሰፍንና የሕዝቡን ሉዓላዊነት የሚያስከብር ነው። እናም ትግሉ ሰላም፣ ብሔራዊ ነፃነትና፤ ዴሞክራሲን ለመትከል ነው። ይህ አንድ ትግል ነው። በሁለተኛ ደረጃ ደግሞ፤ ሁላችንም የምንፈልገው፤ ትግሉ ተሳክቶ ድሉ አስተማማኝ እንዲሆንና የወደፊቷ ኢትዮጵያ፤ እያንዳንዳችን በግለሰብ ደረጃ በእኩልነት ተሳታፊ የምንሆንባት ለማድረግ፤ የወሳኝነት ሚና ለመጫወት ነው።

ከላይ እንዳሰመርኩበት በአሁኑ ሰዓት የተለያዩ የትግል ድርጅቶች መኖራቸውና፤ በተለያዩ የትግል መስኮች የተሰማሩ ታጋዮች መኖራቸው ግልጽ ነው። የዚህ ነባር መሠረታዊ እውነታ፤ አሁን መለወጥ አለበት። የትግሉ ባለቤትና ታጋዩ ሕዝቡ ነው። እናም ዋናው ትኩረት መደረግ ያለበት፤ ሕዝቡ በአንድነት ተሰልፎ እንዲያምጽ መንገዱን መጥረግ ነው። ለዚህም በሕዝቡ መካከል ተገኝቶ፤ የሕዝቡን በደል አብሮ መካፈል ነው። የሕዝቡን ብሶት ማንሳት ነው። በዚህም ከሕዝቡ ጎን ሆኖ፤ ሕዝቡን መከተልና መምራት ነው። ታዲያ መሠረታዊ ተግባር መሆን ያለበት፤ በሕዝቡ መካከል ተገኝቶ፤ ሕዝቡን መቀስቀሱ ነው። ይህ ትግል፤ የገዥውን ወገንተኛ አምባገነን መንግሥት ነጥሎ የሚያወጣና ተግባሩን በግልጽ የሚያሳይ ነው። ይህ ትግል፤ የገዥውን ወገንተኛ አምባገነን ገዥ መንግሥት ሩጫና አስመሳይነት የሚያከሽፍ ነው። ይህ ትግል፤ የአልገዛም ባይነትን ስሜት የሚያበረታታ ነው። ይህ ትግል፤ የታጋዩን መዋቅር የሚያሰፋ ነው። ይህ ትግል የወደፊቱን መጪ ብሩህ እውነታ የሚያስተጋባ ነው። እናም ይህ ትግል በአንድ ኢትዮጵያዊ የነፃነት ንቅናቄ ሥር ተደራጅቶ የሚካሄድ መሆን አለበት።

በአንድነት ተደራጅተን ስንታገል፣ የሕዝቡ የነፃነት ፍላጎት ሲግል፣ ሕዝቡ በየቦታው እምቢተኝነቱን ሲያቀጣጥል፤ ለገዥው ወገንተኛ አምባገነን መንግሥት፤ ሁለት ምርጫ ብቻ ከፊቱ ይደቀናሉ። እነኚህ ወሳኝ የሆኑ ምርጫዎች፤ የገዥውን ቡድን ዕድሜ፣ የሕዝቡን አጸፋ አመላለስና፣ የወደፊቱን የሀገራችን ሕልውና ይወስናሉ። የመጀመሪያው የሕዝቡን ጥንካሬ በመመልከት፤ ለሕዝቡ እምቢተኝነት ተገዝቶ፤ የሕዝቡን ፍላጎት ለሚሟላት ተገዥ መሆን ነው። ሁለተኛው፤ በእብሪት ተሞልቶና **"እኔ ገገር ነኝ፤ እኔ ብቻ ያልኩት መፈጸም አለበት!"** በማለት፤ ጉልበቱን ተጠቅሞ የሕዝቡን እምቢተኝነት በጭካኔ ለመቅጨት፤ ሠይፉን ከአፎቱ መምዘዝ ነው። የመጀመሪያው እንደሂደቱ የሚመለስ ሲሆን፤ የተለመደው የአምባገነኖች መጨረሻ እንዳስገነዘበን ግን፤ የሁለተኛውን ምርጫ ነው መጠበቅ ያለብን። ያኔ የሕዝቡ የአጸፋ መልስ፤ የገዥው በእብሪት ጉልበት መከላከልና የበላይነቱን ለመጠበቅ የሚያደርገው ሩጫ፤ የወደፊቱን ይወስናል። ለሕዝቡ ያኔ የሕልውና ግዴታ ቦታውን ይወስዳል። በአንድ ተደራጅተንና ጠንክረን ስንገኝ፤ በመኖርና ባለመኖር መካከል ለሚቀመጥ ሕልውና፤ በማናቸውም መንገድ መኖርን በመምረጥ መቆማችን፤ አጠያያቂ አይደለም። ከወዲሁ በመተንበይ፤ አፈጻጸሙ እንዲህ ወይንም እንዲያ ይሆናል ባንልም፤ በሂደቱ፤ ይሄ ጠንካራ የኢትዮጵያዊያን የነፃነት ንቅናቄ፤ ትክክለኛ መልስ በመሥጠትና አስፈላጊውን የትግል መንገድ መርጦ በመሄድ፤ ድሉ የሕዝቡ እንደሚሆን፤ ጥርጥር ሊኖረን አይገባም።

አዎ ዛሬ በሀገራችን የሕግ የበላይነት የለም። የጉልበት ግዛት ሠፍኗል። ወንጀል መሥራት ሳይሆን፤ ኢትዮጵያዊ ሆኖ መገኘትና ኢትዮጵያዊ ነኝ ማለት፤ ያስወነጅላል። በሰላም ሠርቶ ማደር ያስወነጅላል። ለሀገርና ለወደፊቱ መቆርቆር ያስወነጅላል። እናም ሕዝቡ ይኼስ በዛ ብሎ ተነስቷል። ሕዝቡ ኢትዮጵያዊ ነኝ ብሎ ቆሟል። አንድ ኢትዮጵያዊነት ነው ያለው። እናም ሕዝቡ በአንድነት ነው የሚታገለው። ለድርጅት ሳይሆን ለኢትዮጵያዊነቱ ነው የሚታገለው። የትግል አንድነቱ እስከተፈጠረ ድረስ፤ በጊዜው ስለሚደረገው ትግልም ሆነ ስለአካሂያዱ አሁን መዘርዘሩ ዋጋ የለውም። እስኪ መጀመሪያ የትግል አንድነቱን እንፍጠር። የድርጅቶች ሁሉ የቅድሚያ ተግባር፤ አንድነት መፍጠሩ ይሁን።

የመጨረሻውን ከየት እንጀምር? የሂደቱን ዝርዝር በሚቀጥለው አቀርባለሁ።

eske.meche@yahoo.com
http://nigatu.wordpress.com